# “ እውይ ልማድ! የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ትምህርት አስተማሪው ተቃወሙ !”

ቀን Dec 16/2014

እምሩ ከለገጣፎ

“ውይ ! አምባሳደሩ ተናገሩ !”የሚለውን ርእስ ሳይ የልጅነት የብሽሽቅ ጨዋታችንን ለአፍታ አስታወሰኝ። ወደውስጥ ገብቼ ለማንበብ ስጀምር የዛሬ 30 አመት …ሳስተምር… አይኔን አላመንኩም።እድሜው ከ60 አመት የዘለለ አዛውንት እቃ እቃ ሲጫወት! ለ“ውይ”! አምባሳደሩ ተናገሩ ! ለሚለው ርእስ ምላሽ ለመስጠት የሚሆን ርእስ ስመርጥ ከልጅነት እድሜ ብዘልም ግልገል ጎሮምሳ በመሆኔ የ“ውይ!” አምባሳደሩ ተናገሩ ! ፀሃፊን ስላቅ መበደር ፈለኩኝ።ተበድሬም አልቀረሁ “ውይ! የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ትምህርት አስተማሪው ተቃወሙ! ” ብዬ ከነወለዱ ከፈልኩኝ።

አቶ ወንድሙ መኮንን ! ዶ/ር ወንድሙ መኮንን ሊሆንም ! ይችላል ።እርስዎ እንዳልልዎት ከገለባም ቀልለው ተገኙብኝ። አንተ! እንዳልል ደግሞ እድሜ ጠገብ ሆነው አገኘሆት። በዚያ ላይ ምሁር ! አስተማሪ ! መምህር! አስተዳደጌ ደግሞ ለአስተማሪ ፥ ለመምህር ትልቅ አክብሮት አለው። መምህር በእድሜው ትንሽ ቢሆንም እንኳን “እርስዎ” በሉ ብለው ነው ወላጆቼ ያስተማሩኝ። እናም የታናሽዎ ታናሽ ታናሽ ብሆንም ውርጋጥ ግን አይደለሁም።ምንም ያህል “ጨዋ ምሁር” ባይሆኑም “መምህር” እና “አዛውንት” በመሆንዎ ብቻ እርስዎ ብዬዎታለሁ።

መምህር ሲባል ምንጊዜም ትዝ የሚለኝ “ረቡኒ” የሚለው የመፅሃፍ ቅዱስ መምህር ነው። በጥላቻ ፋንታ ፍቅርን፥ በሃሰት ፋንታ እውነትን፥ ከሞት ይልቅ ህይወትን፥ ከጨለማ ይልቅ ብርሃንን ፥ከመውቀስ ይልቅ መምከርን የሚሰብከውና የሚያስተምረው። የኛ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ትምህርትአስተማሪ ግን በተቃራኒው በፍቅር ፋንታ ጥላቻን፥ በእውነት ፋንታ ሃሰትን፥ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን፥ ከጥበብ ይልቅ ድንቁርናን ባልተገራ ብእርዎ ሲተፉት ሳይ እውይ ! አዛውንት! እውይ ! ምሁር አልኩኝ። ከምሁርነት ይልቅ የተረት አባትነት አይሎብዎታል። ውይ አባባ ተስፋዬ !

አባባ ተስፋዬስ ካረጁ በጁ ! ምነው "ዶ/ር" መኮንን ካረጁ አልበጁሳ !? "ስደት" ይሆን እንዲህ ያረግዎት ወንድምዬ!? ወይንስ የቁጥር ትምህርት መላቅጡ ጠፋብዎ!? የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ማለቴ ነው:: ያደረ ሂሳብ በቅጡ አልተወራረደልዎትም መሰለኝ::

ወንድምዬ እድሜ እኮ ጸጋ ነው::ላደለው እድሜ መከበሪያ÷መታፈሪያ÷ መሸምገያ÷ ማስታረቂያ÷ ጥበብና እውቀትን ለተከታዮቹ ማሸጋገሪያ÷አዲስ እና ብሩህ ትውልድ መፈጠሪያ÷ለሃገሩ እና ለወገኑ ደግሞ ካካበተው ቁምነገር ተሞክሮውን ማካፈያና ስም ማስጠሪያ ነው::እባክዎን እስኪ ሃቁን ይንገሩን እና በሂሳብ መዝገብ አያያዝ ትምህርት ባለሙያነትዎ ምን ሰሩበት ? እነማንን አፈሩበት? ለሃገርዎ ምን ፋይዳ ፈየዱበት ? እሺ ! ቁምነገር ይቅርብዎት እንበል:: ቁምነገር በዋለበት ቦታ የዋሉ አይመስሉምና:: ታዲያ ስድብን ምን አመጣው !? ነው ወይንሰ መምህርነትዎ በጥላቻና በጥርጣሬ የተሞረደ ሆኖ ነው? ያደለው በእድሜ ባለጸጋነቱ ስንት ቁምነገር ሲሰራበት የርስዎ ቢጤው ደግሞ የጆሮ ጉትቻ ÷ ያንገት ጌጥ ÷ ምርጥ የሳሎን እቃ አደረገውሳ !? ጽሁፎን ሳነብ ከሶስት አስርት አመታት በፊት ከራሱ ገበታ ተሻግሮ የሰው ገበታ ላይ ጆሮውን ጣል አድርጎ ተረት ተረት እንደዋዛ የሚቀላውጥ ÷ ከሶስት አስርት አመታት በኋላ የቀላወጠውን ተረት መልሶ የሚተርክ ዋዘኛ÷ እድሜና ዘመን የማይለውጡት÷ ታሪክ ወይንም ተረት ሳይሆን አሉባልታ ሰናቂ÷ ዛሬ ላይ ሆኖ ከ30 አመት በፊት የተቀመጠበትን የምግብ ቤት ጠረጴዛና ወንበር ላይ ያለ÷ እድሜው በቁጥር እና በሽበት የጨመረ÷ ግን ደግሞ ተጋግሮ ያልበሰለ ሊጥ÷ ተጥዶ ያልደረሰ ÷በተሃ ÷ስለለውጥ ህግጋት ያልገባው ÷ ወይንም ገብቶት አይኑ የማያይ÷ ጆሮው የማይሰማ "ምሁር" እና "መምህር":: ምላሱ ደግሞ የሚሰራን ለመወረፍ ከብርሃን ፍጥነት በላይ የሚጓዝ ÷ ሰው በምላሱ ስንት ይሰራበታል አለች ሴትየዋ እንዲሉ አረ ወንድምዬ በምላስዎ ደግ ደጉን ይስሩበት:: ምክር ማለት ይሂ ነው ከተስማማዎት::

ወንድምዬ ለመሆኑ "ዲፕሎማሲ" ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቀ ገበቶዎታል ይሆን!? "ዲፕሎማት" ማለትስ? በቀላል እና ግልጽ ቃል ዲፕሎማሲ ጥበብ ማለት ነው:: ጥበቡ ደግሞ የአገሬ ሰው እንደሚለው "ዋሽቶም ቢሆን ማስታረቅ " እንደ እርሰዎ ዋሽቶም ቢሆን ማጣላት አይደለም:: ዲፕሎማት ደግሞ "ምርጥ እቃ" ማለት ነው:: ነገሩ በደንብ ከገባዎ ማለት ነው::እንደ እርሰዎ ቀዳዳ እቃ ሳይሆን::እውን ታሪካቸውን የተረኩልንን

የኢትዮጵያ ምርጥ እቃ-ክቡር አምባሳደር ብርሃኑ ከበደን- በቅጡ ያውቋቸዋልን!?እርሰዎ የገለጿቸው አይነት ሰውስ ናቸውን!?እንደ እርሰዎ ያለው ቀዳዳ እቃ የሚመከራቸውስ ናቸውን!? በምንሊክ ጊዜ ያበደ ምንሊክ ይሙት እያለ ይቀራል አሉ ተራቾች:: ሃቁን የሚያውቁት ከሆነ አሁንም በድጋሚ ይስሙት:: ካላወቁት ደግሞ ይወቁት:: አልሰማም አላይም ካላሉ በስተቀር::

ክቡር አምባሳደር ብርሃኑ ከበደ እምዬ ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው የምርጦች ምርጥ ዲፕሎማት፥ በሙያቸው ባካበቱት ልምድ ለአገራቸው ብሄራዊ ጥቅም መከበር በሚያደርጉት ተጋድሎ የስራ ባልደረቦቻቸው የሚያከብሯቸው፥ አለቆቻቸው የሚያደምጧቸው ፥ በጓደኞቻቸው ዘንድ ተወዳጅ ፥ ለቤተሰቦቻቸው እና ለወገናቸው ደግሞ መኩሪያ ናቸው:: አምባሳደሩ ደከመኝ እና ሰለቸኝን በታሪካቸው የማያውቁ፥ እውቀታቸውን፥ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን መተኪያ ለሌላት ለውድ እናት አገራቸው በማዋል ላይ ያሉ፥ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ተሳስበው የሚሰሩ እና በርካታ ወጣት ዲፕሎማቶችን ያበቁ ምርጥ እቃ ናቸው:: ይህንን ወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ እንደ እርሰዎ ያለ ቀዳዳ እቃ እና "ጠላት" ጭምር የሚመሰክረው ነው:: ከራስዎ በማስፈቀድ ልጥቀስ ::

*"ትልቁ ነገር ግን በኢትዮጵያ ኢንቨስት የሚያደርጉ ኢንቨስተሮች ትልልቆች ናቸው፡፡ ለአብነት ለመጥቀስ ዲያጆ የሚባለው በኢትዮጵያ ውስጥ በ225 ሚሊዮን ዶላር ሜታ ቢራ ፋብሪካን ገዝቷል፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ 100 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስት አድርጓል፡፡ ስለዚህ በአጠቃላይ 325 ሚሊዮን ዶላር ኢንቨስትመንት አለው ማለት ነው፡፡ ዩኒሊቨር የሚባለው ትልቁ የመልቲላተራል ኩባንያ በኢትዮጵያ ውስጥ የመጀመርያ የኢንቨስትመንት ኦፕሬሽን እየጀመረ ነው ያለው፡፡ ሦስተኛ ፒተርድ የሚባለው የቆዳ ውጤቶች አምራቾች ድርጅት ለሰባ ዓመታት ጥሬ ቆዳ ይገዛ የነበረው በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሦስት ፋብሪካዎች ሠርቶ ከ1,500 እስከ 2,000 ሠራተኞች ቀጥሮ እያሠራ ይገኛል፡፡ ይኼም የታወቀ ብራንድ ስለሆነ የቆዳ ውጤቶቹ ብሪቲሽ ኤርዌይስ የሚጠቀምበት ትልልቅ ሱቆች ውስጥ እየገባ ነው፡፡ ሌላ በማዕድን ፍለጋ ስንሄድ ታሎ በነዳጅ ፍለጋ ኢትዮጵያ ውስጥ ትልቁ ካምፓኒ ነው"*

አሁንም ይሄ የሚያሳየው አምባሳደሩ በተሰለፉበት ስራ ውጤታማ መሆናቸውን ነው::ወንድምዬ! እኔስ የቁም ሞት ብቻ መስለው ነበር፥ ለካስ ምንስ ጥላቻ ቢመርም ሃቅ ተደብቃ አትቀርምና እውነቱን ገልጠው ለመናገር ደሙ-ነብስዎም ቢሆን ወትውታዎታለች::

አምባሳደሩ አንዴ ከጀርመን ራዲዮ ድረስ ደውለው ፥ ሌላ ጊዜ ቪኦኤ ደውለው እያሉ ይከሷቸዋል:: የዲፕሎማሲ ሙያ በር ከርችሞ ራስንም መከርቸም አይደለም::ወይንም እንደ ብቂ ባህታዊ በር ዘግቶ በጾምና በፀሎት ራስን መወሰን አይደለም::ዲፕሎማሲ ጥበብ ነው ብዬዎታለው::ጥበብነቱ ደግሞ የተዘጋን በር ማንኳኳት ና ማስከፈት፥ በተከፈተ በር መግባት፥ የገቡበትን አላማ ማስረገጥ፥ ልዩነቶችን ማጥበብ፥ የአንድን ወገን ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ወገን ታሪክ ሰምቶ የራስን አቋም እንዲወስድ ማስቻል ነው:: ይህን ካልን አምባሳደሩ ጠይቀውም ይሁን ተጠይቀው በርካታ በሮችን አንኳኩተዋል፥ ገብተዋል፥ የመንግስታቸውን አቋም ይፋ አድርገዋል፥ የአገራቸውን ብሄራዊ ጥቅም አራምደዋል:: ይህ ደግሞ ለእርስዎና ለመሰሎችዎ ራስ ምታት ሆኖባችኋል:: በር የሚያንኳኳ ሳይሆን የሚያንቀላፋ ዲፕሎማት ከተገኘላችሁ መደላድላችሁ ስለሆነ ብቻ::የእርሰዎ የበግ ለምድ የለበሰ ቀበሮ ባህታዊ “ምክር” (ቀዳዳ እቃ ለመምከር ባይበቃም) አገራቸውን ከድህነት እና ከውርደት ለማላቀቅ ቀን ከሌሊት ደፋ ቀና የሚሉትን ምርጥ የእምዬ ኢትዮጵያ እቃዎችን መቼም ቢሆን አያሸማቅቅም::

ወንድምዬ ኢትዮጵያ እያሉ የተማሩባቸው ት/ቤቶችና ያስተማሩበት ዩኒቨርሲቲ በእርስዎ ዘመን የተሰሩ ሳይሆኑ አባትዎ እና አያትዎ የሰሯቸው መሆናቸውን የሚዘነጉት አይመስለኝም::አሁንም ቢሆን እውነተኛ እና ሃቀኛ ኢትዮጵያዊያን ለአሁኑም ሆነ ለሚመጡት ትውልዶች የሚሆኑ ቋሚ ቅርሶችን እንሰራለን:: የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ እናንተ ልጆቹን የፈረንጅ ት/ቤት እየላከ፥ ከፈረንጅ ሱፐርማርኬት እየሸመተ፥ ቤተሰብ እየመገበ፥ በየፈረንጁ ጎዳና ተኮልኩሎ ለኢትዮጵያ የልማት እርዳታ አትስጡ እያለ ዳያስፖራውን የሃሰት ፕሮፓጋንዳ እያጋተ አገርህን አትመልከት፥ ውዱ ህዝባችንን እርስ በእርስ የሚያጋጭ የዘረኝነት ጥላሸት እየቀባ አንዱን በሌላው ላይ የሚያነሳሳ ሳይሆን አዲሲቷን ኢትዮጵያ በብሄር፥ በሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት ላይ እየገነባ ድህነትን ታሪክ አድርጎ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር በጉዞ ላይ ያለ አኩሪ ትውልድ ነው::ኢትዮጵያችን አሳዳሪ ጌታ የላትም::እርስዎና መሰለችዎ እንደናፈቃችሁ ይቅርና ያ ዘመን ዳግም ላይመለስ በኖ ጠፍቷል::ኢትዮጵያችን አሳዳሪ ጌታዋ ህዝቦቿ፥ብሄር ብሄረሰቦቿ ናቸው:: እባክዎ ከተኙበት ይንቁ:: ጉዟችን ረጅም ግባችንም ሩቅ መሆኑን አይዘንጉት::

ልጨምርልዎ! በተባበረ የኢትዮጵያዊያን ጥረት ታላቁ የህዳሴ ግድብ ይገነባል:: የሚያቆመው አንዳችም ሃይል የለም::እርሰዎ “የውስጥ አዋቂው” እንዳሉት ህዝቡ ተታሎና ገንዘቡ ተሞሽልቆ የቀረ ሳይሆን ከ40 በመቶ በላይ የግድቡ ስራ ተጠናቋል::ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ፋይዳ ያላቸው በርካታ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች በሂደት ላይ ናቸው:: ዝርዝሩን ብጀምረው ስለማልጨርሰው ባልነካካው ሳይሻል አይቀርም::

“መምህር” ሆይ! ደግመው ደጋግመው ወያኔ! ወያኔ! ማለት አበዙሳ:: አቤት ሲፈሩት!! ቃሉን ወይንስ...!?ለመሆኑ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ተሳትፈው ይሆን!? ወይንስ እንደ እኔው በንባብ ብቻ ነው ያገኙት? ስለኢትዮጵያ ገበሬዎች አመጽ ምን ያህል ተገንዝበው ይሆን? አዋቂነትዎን እየጠየኩ ሳይሆን እንደ ተዋናይት ማክዳ ሃይሌ ስለ ወያኔ አመጣጥ ታሪካዊ ማብራርያ ልስጥበት ብዬ ነው:: ምናልባት ጊዜ ከሌልዎ በሚል ስጋት ባጭሩ ወያኔ እንደ ራያ ሰዎች አባባል ወይ አነ ! ወይኔ! ማለት እና ቁጭትን መግለጫ ሲሆን በተራማጆች ቋንቋ አብዮት ማለት ነው:: ወያናይ ማለት ደግሞ አብዮተኛ! ታጋይ! ጀጋኑ ! ጀግና! ማለት ነው:: በቃ:: ይሄው ነው::

በ1940 የትግራይ ገበሬዎች ለአመፅ ሲነሱ የመጀመርያ የወያኔ አመፅ የሚል ስያሜ ተሰጠው:: ይህ ትግል ደግሞ አሁን እርሰዎ አውቀውት ይሁን አጥተውት ወያኔ እያሉ የሚደጋግሙትን እንቅስቃሴ ወልዶ ትግሉ ተሳካ! ፍሬም አፈራ! የዘር ፖለቲካ እያሉ ለመቀስቀስ የሚጠቀሙበት አገላለፅም ያለቦታው የተቀመጠ ይመስለኛል:: የዛሬው አንቀፅ 39 የህዝቦች የዘመናት የትግል ውጤት መሆኑን አይዘንጉት:: እንዳነበብኩት ከሆነ ድሮ ተማሪዎች የታገሉት “መሬት ላራሹ”፣ “የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት”፣ “የኤርትራ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ ይወስን” የሚሉ መፈክሮችን አንግቦ መሰሎኝ?:: ከተሳሳትኩ እንደ መምህርነትዎ በስድብ ሳይሆን በጨዋ ቋንቋ ያርሙኝ:: እኔ ለመማር ዝግጁ ነኝ:: ኢሃዴግም ይህንኑ ነው ለኢትዮጵያችን ያበረከተው::

ስለሰብአዊ መብት “ነፃና ታማኝ” ስለሚሏቸው ሚዲያዎች እና የሰብአዊ መብት ተሚጋች ደርጅቶች የዘበዘቡትንም አነበብኩ:: ተረት!ተረት! መቼም የሰብአዊ መብት ተሚጋች ደርጅቶች ያሏቸው ሁለት ስለት ያለው ቢለዋ መሆናቸውን ለእርስዎ መንገር የለብኝም::ልጅ እናትዋን ምጥ አስተማረች ይሆንብኛልና::ጓንታናሞ የሰብአዊ መብት ጥበቃ አለ ይበሉኝ ወንድምዬ:: ጋዛ የሰብአዊ መብት ጥበቃ አለ ይበሉኝ እባክዎን:: ግብፅና ኤርትራ መካከለኛው

ምስራቅ የሰብአዊ መብት ጥበቃ አለ ይበሉኛ::የመብት ተሟጋቾች የተጠቀሱትን አገራት ውጉዝ ከመአርዮስ አድርገዋቸዋል ይበሉኛ:: ጋዜጣዎቹ አዳልተው አያውቁም ይበሉኛ::

የእርዳታ ፕሮግራም ስረዛ አሉኝ ወንድምዬ ! በእርግጥ እኔ እንደእርስዎ ውስጥ አዋቂ አይደለሁም:: ምክንያቱን ብትን ብትንትን አድርጌ እንደእርስዎ አላውቅም :: እርዳታ ሰጪዎቹ ከእኔ ይልቅ ለእርሰዎ ስለሚቀርቡ:: አንድ የማውቀው ሃቅ ግን አለ::አገር በእርዳታ አታድግም::እርዳታ ቋት መሙያ ነው::ነፃ እርዳታ የሚባል ነገር የለም::እርዳታ ሰጪው ከእርዳታ ተቀባዩ አገር የሚፈልገው የሚታይም ሆነ የማይታይ ተከፋይ ዋጋ አለ::እርዳታ መቆንጠጫ መሆን ያለበት አይመስለኝም::እንደ "ተመሳሳይ ፆታ ግንኙነት ካልፈቀድክ እርዳታዬን አቆማለሁ"፥ "ዲሞክራሲን ካልተገበርክ እርዳታዬን እነፍጋለሁ"፥ አንዳንዴ እንደ ነዳጅ ከበርቴዎች አገራት ቢያደርገንስ እላለሁኝ:: የምን የሰው እኩልነት? የምን የፆታ እኩልነት?የምን ዲሞክራሲ? ብቻ ለለጋሾቻችን መመቸት:: ክስ የለብህ ፥ ዳኛ የለብህ፥ እንደውም የውሾን ነገር ያነሳ ይባልልሃል::ኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት እና የህግ የበላይነትን የምታከብረው፥ዲሞክራሲያዊ ስርአትን የምትገነባው፥ የሚዲያ ነፃነትን የምታከብረው፥ ለእነ ተረት ተረት አባት ብላ ሳይሆን፥ለለጋሾችና አበዳሪዎች ብላ ሳይሆን እነዚህ መብቶች ህገመንግስታዊ ከለላ ያላቸው በመሆኑ፥ኢትዮጵያ አለም አቀፉ ማህበረሰብ የፈረማቸውን መብቶች ፈራሚ በመሆኗ፥የነዚህ መብቶች አለመከበርና መጣስ የተጀመረውን አገራዊ ልማት የሚያጓትተው፥የድህነት ቅነሳ ትግሉን አደጋ ላይ የሚጥለው በመሆኑ ብቻ ነው::ኀዳናው ተጠርጓል፥ ዘመቻው ተጧጡፏል፥ወድቀን እየተነሳን የተመፃደቁበትን ስርአት እንገነባለን::

ወንድምዬ!ኢትዮጵያችን በእርሰዎ እና በመሰልዎችዎ ጩሀት አትበረግግም፥ኢትዮጵያን ለማፍረስ የሚነሳ ማንኛውም ሽብርተኛ ይዋል ይደር እንጂ የእጁን ማግኘቱ አይቀርም::የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት የአገሪቱን ሉአላዊነት ሊረግጡና ህገመንግስታዊ ስርአቱን በአመፅ ሊጥሉ የሚነሱ የጥፋት ሃይሎችን በህጋዊ መንገድ አደብ ሊያስገዟቸው ሃላፊነት እና ግዴታ አለባቸው::እርሰዎ በፅሁፍዎ የዘረዘሩዋቸው የእርስዎ ብቻ "አርበኞች" ለኢትዮጵያ ህዝብ እና መንግስት ደግሞ ነውጠኞች እንዲሁም መሰሎቻቸው ይዋል ይደር እንጂ ለፍትህ መቅረባቸው አይቀሬ ነው::የእርሰዎ እና

መሰሎችዎ "ጀግንነት" ህዝብ የመረጣቸውን ወኪሎች መሳደብና ማዋረድ፥ብሎም በአውሮፓ ጎዳናዎች ላይ መውረግረግ ቢሆን አይደንቀንም።ብቻ ነገሩ የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም ሆኖ ማሳዘኑ ነው እንጂ። እናነተም ተሳደቡ፥ጩሁ፥ደንሱ፥ኢትዮጵያችንም ግሰጋሴዋን ትቀጥላለች።

ቸር ያሰማን

e_emiru@yahoo.com